

# ደስታ ፡ ቀላል ፡ ነው ፤

እኔን ፡ ደስ ፡ ብሎኛል ፡ እንኳን ፡ አላችሁ ፣
በውጭ ፡ አገር ፡ ስደት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያላችሁ ፣
የምሥራች ፡ ምስር ፡ ብሉ ፣
ተጠራርታችሁም ፡ ተባባሉ ፤
እግዜር ፡ ይማርዎት ፡ ሰማን ፡ ወሬውን ፣
ከቀዶ ፡ ጥገና ፡ ማገገምወን ፣
የጀመሩት ፡ ሥራ ፡ ምኀንድሳውን ፣
ኢትዮጵያን ፡ ለማልማት ፡ ለመርዳት ፡ ሕዝቧን ፣
ኃይሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነው ፡ ሊያስፈጽምልን ፣
በፍጹም ፡ ልባችን ፡ እንመኛለን ። እንጸልይ ፡ አለን ።
ኮረንቲ ፡ መልእክቱን ፡ በጣም ፡ ወደደኩት ፣
ጭንቀቴም ፡ ቀለለኝ ፡ የተሸከምኩት ፣
ስለኃይሉ ፡ ሻውል ፡ እያማጠንኩት ፣
እንዳያሳፍረን ፡ እየለመንኩት ፣
ደስ ፡ አለኝ ፡ ለግዜው ፡ ተምስገን ፡ አልኩት ።
እጆቿን ፡ ዘርግታ ፡ የምትለምነውን ፣
ምንግዜም ፡ አይረሳት ፡ እግዜር ፡ ኢትዮጵያን ፣
ይኸው ፡ እያየን ፡ ነው ፡ ሲረዳ ፡ ልጇን ፣
ሕዝብን ፡ አስተባብሮ ፡ ሊጠር ፡ እናቱን ፣
ደፋ ፡ ቀና ፡ እያለ ፡ ቆላ ፡ ደጋውን ፣
ቅንጅት ፡ መሥርቶ ፡ የሚደክመውን ፣
ጅምሩን ፡ ሊጨርስ ፡ የተለመውን ፣
ታሞ ፡ እንኳን ፡ ሳይሰለች ፡ አይዟችሁ ፡ ሲለን ፣
እንዴት ፡ ጤና ፡ እያለን ፡ ዝም ፡ እንላለን ።
እናሰማ ፡ እልልታ ፡ አለንልህ ፡ ብለን ፣
በበለጠ ፡ ድኖ ፡ ቶሎ ፡ እንዲወጣልን ፣
ከሐኪም ፡ ቤት ፡ አልጋው ፡ ተንሥቶ ፡ እንዲታየን ፣
እየተዟዟረ ፡ ሲፈጽም ፡ ሥራውን ።
ደስታ ፡ ቀላል ፡ ነው ፡ እንዳትዘናጉ ፣
ትግላችን ፡ ይጠንክር ፡ ለወግ ፡ ለማረጉ ፣
ሰላም ፡ እንዲሰፍን ፡ ጠላት ፡ ደስ ፡ እንዳይለው ፣
እንበርታ ፡ በርቱ ፡ ኃይሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነው ፣
ምንም ፡ ነገር ፡ የለ ፡ ጸሎት ፡ የማይፈታው ፣
ይላልና ፡ ሕዝቡ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያለው ፣
ቅንጅት ፡ ፍቅር ፡ ነው ፡ መሪያችን ፡ ኃይሉ ፡ ነው ፣
ሻውል ፡ ነፍሱን ፡ ይማር ፡ እሱን ፡ ያስወለደው ።

በእግዚአብሔር ፡ እርዳታና ፡ በልጆቿ ፡ ብርታት ፡ ኢትዮጵያና ፡ ቅንጅት ፡ ያሸንፋሉ ። አሜን ። ሃሌ ፡ ሉያ ።

ኅዳር ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፳፻ ፡ ዓመት ፡ ምሕረት ፤

ስለሺነህ ፡ ገላነህ ፣
ኩቤክ ፣ ካናዳ ።